Amharic

Instructions for Collecting Sputum for TB

# ለነቀርሳ ምርመራ የአክታ ማጠራቀሚያ መመሪያ

## የአክታ ምርመራ ለምንድነው የሚያስፈልገው?

ዶክተርዎ ሲያስሉ ከሳምባዎ የሚወጣውን አክታ መውሰድ ይፈልጋል። ላቦራቶሪው የተወሰደውን አክታ የነቀርሳ ጀርሞች እንዳሉት ይመረምራል።

የነቀርሳ በሽታ እንዳልዎት ለማወቅ አክታን ማስመርመር ጠቃሚ ነው። የነቀርሳ መድሃኒት እየወሰዱ ከሆነ አክታዎን በመመርመር መድሃኒቱ እየሠራ መሆኑን ማወቅ ይቻላል።

ምርመራው ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አክታውን ከውስጥ ከሳምባዎ ስለው ማውጣት አለብዎ። ከሳምባ የሚወጣ አክታ ብዙ ጊዜ ወፍራምና ዝልግልግ ነው። ምራቅ ግን ከአፍ የሚመጣና ውሃማና ቀጭን ነው። ምራቅ አይስጡ።

**ዘዴ፦ አክታ አስሎ ማውጣት ካቃትዎት ከሙቅ ሻወር ወይም ከተጣደ የሚፈላ ውሃ የሚወጣውን እንፋሎት ወደ ውስጥ ይተንፍሱ።**

## አክታ እንዴት እንደሚጠራቀም

ዶክተርዎ ወይም ነርስዎ ለአክታ ማጠራቀምያ የሚሆን ልዩ የፕላስቲክ ብልቃጥ ይሰጥዎታል። የሚከተሉትን ነጥቦች በጥንቃቄ ይከተሉ፦

1. ብልቃጡ በጣም ንጹህ ነው። ለመጠቀም ዝግጁ እስከሚሆኑ ድረስ አይክፈቱት።
2. ጠዋት እንደነቁ (ምንም ነገር ከመብላትዎ ወይም ከመጠጣትዎ በፊት) ጠርስዎን ቦርሹና በውሃ አፍዎን ይግሞጥሞጡ። የአፍ መታጠቢያ (mouthwash) አይጠቀሙ።
3. ከተቻለ አክታውን ከማጠራቀምዎ በፊት ወደ ውጭ ወጣ ይበሉ ወይም መስኮት ይክፈቱ። ይህ በሚስሉበት ጊዜ ሌሎችን ሰዎች ከነቀርሳ ጀርም ይከላከላቸዋል።
4. ወደ ውስጥ አየር ስበው ለ5 ሴኮንዶች ይያዙት። ቀስ በቀስ ወደ ውጪ ይተንፍሱ። እንደገና ወደ ውስጥ አየር ይሳቡና አክታ ወደ አፍዎ እስከሚመጣ ድረስ በደንብ ይሳሉ።
5. አክታውን የፕላስቲክ ብልቃጥ ውስጥ ይትፋት።
6. አክታው 5 ml የሚለው መስመር ላይ እስከሚደርስ ድረስ (ወይም ከዛ በላይ) ይህንን ማድረግ ይቀጥሉ። ይህ አንድ የሻይ ማንኪያ አክታ ይወጣዋል።
7. እንዳይፈስ አድርገው ክዳኑን አጥብቀው ይክደኑት።
8. የብልቃጡን ውጪውን አጥበው ያድርቁት።
9. ብልቃጡ ላይ አክታውን ያጠራቀሙበትን ቀን ይጻፉበት።
10. ብልቃጡን ነርስዋ የሰጠችዎት ሳጥን ወይም ከረጢት ውስጥ ይክተቱት።
11. ብልቃጡን ለነርስዎ ወይም ለክሊኒክዎ ይስጡ። ካስፈለገ ብልቃጡን ፍሪጅ ውስጥ ማሳደር ይችላሉ። በረዶ መስሪያ ውስጥ ወይም ከውጭ አይተውት።

Oregon Health Authority

Adapted from material from the Minnesota Department of Health, TB Prevention and Control Program